በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

16/2005

711/2013

የለውጥና የልማት ቡድን አደረጃጀት መመሪያ

ቁጥር 711/2013

መስከረም 2005

ከ/ል/ኮ/ሚ

ማ ው ጫ

ገጽ

መግቢያ 1

ክፍል አንድ 2

አጠቃላይ ሁኔታዎች 2

1. አጭር ርዕስ 2

2. ትርጓሜ 2

3. አስፈላጊነት 3

4. ዓላማ 3

5. የሚጠበቅ ውጤት እና ፋይዳ 4

6. የተፈፃሚነት ወሰን 5

ክፍል ሁለት፡ 5

የለውጥና የልማት ቡድን አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት 5

7. የአደረጃጀት ሁኔታ 5

8. የለውጥና የልማት ቡድን ተግባርና ኃላፊነት 6

9. የለውጥና የልማት ቡድን አስተባባሪ ተግባርና ኃላፊነት 7

10. የመምሪያ ኃላፊ 8

11. የቢሮ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት 9

12. የማስፈፀም አቅም ግንባታና የለውጥ ስራ አመራር ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት 10

13. የሚኒስትር ዴኤታ ተግባርና ኃላፊነት 10

14. የሚኒስትር ተግባርና ኃላፊነት 11

ክፍል ሦስት 11

የለውጥና ልማት ቡድን አሰራር ሁኔታ እና አካሄድ 11

15. የውይይት ጊዜ ሰሌዳ 11

16. የውይይት መድረኩ አካሄድ እና አፈፃፀም 12

17. የለውጥና የልማት ቡድን መረጃዎች አያያዝ ሁኔታ 13

18. የግንኙነት አግባብና ሪፖርት 14

ክፍል አራት 14

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 14
19. የለውጥ እና ልማት ቡድን የማስፈፀም ኃላፊነት 14
20. የያታ አገላለጽ 14
21. መመሪያውን ስለ ማሻሻል 15
22. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ 15

መግቢያ

በሚኒስቴር መስሪያቤታችን የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎቻችንን ስኬታማ ለማድረግና የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን በተሟላ መልኩ ለማሳካት የመፈፀም አቅማችንን መገንባት እጅግ አስፈላጊ ሲሆን የመፈፀም እና የማስፈፀም አቅም ተገነባ የሚባለው ደግሞ መንግስት የነደፋቸውን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና የልማትና የዴሞክራሲ ዕቅዶችን በብቃትና በጽናት መፈፀም የሚችል እንደ አንድ አካል የሚንቀሳቀስ የለውጥ ሠራዊት ኃይል መፍጠር ሲቻል ነው። ስለዚህ የምናከናውናቸውን የልማትና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶችንና ግቦችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስፈፀም በተቀናጀ መልክ ሚናቸውን በብቃት መወጣት የሚችሉበት የለውጥና ልማት ቡድን በመገንባት ነው።

የለውጥ ሠራዊት በተቋሙ መገንባት ያስፈለገበት መሰረታዊ ምክንያት የለውጥ ስራዎችን በውጤታማነት ለመፈፀም ያለመ ሲሆን የሚገነባው የሚኒስቴር መስሪያቤቱ የለውጥ ሠራዊት በአመለካከቱ፣ በክህሎቱና በእውቀቱ የተሟላና ባስተሳሰብ የተለወጠ በፀረ ድህነት ትግሉ ላይ በግንባር ቀደምነት በመንቀሳቀስ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችንን በመፈፀም የህዳሴውን ጉዞ እውን ለማድረግ ቆርጦ የተነሳ ሠራዊት ለመፍጠር ነው። ለዚህም የለውጥ ሠራዊቱ ሚኒስቴር መስሪያቤቱ በጀመራቸው በድህነት ላይ የሚደረጉ ዘመቻዎችና የስርዓቱ አደጋ በሆነው በኪራይ ሰብሳቢነት ላይ ለሚካሄደው ትግል ድጋፉን ከመስጠት እና በዘርፉ የተያዘውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን በተደራጀ መንገድ እንዲፈፀም ያስችላል።

ስለዚህም አመራሩንና ሰራተኛውን በከፍተኛ ደረጃ አንቀሳቅሶ ቀጣይነት ያለው የዕቅድ አፈፃፀምና የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ የአመራሩና የሰራተኛው ክህሎት እንዲሻሻል፣ እንዲሁም በየደረጃው የሚያጋጥሙትን ማነቆዎች መፍታት እንዲቻል ብቃት ያለው አመራርና ፈፃሚ የመፍጠር ሥራ የመንግስት ግንባር ቀደም ስራ ነው።

ይህንኑ እውነታ ታሳቢ በማድረግ በሚኒስቴር መስሪያቤቱ በየደረጃ ያሉ አመራርና ፈፃሚ አካላትን በለውጥና ልማት ቡድን በማደራጀት በተለየ ኃላፊነትና ቁርጠኝነት እንዲንቀሳቀሱ የተለየ ግንባታ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ክፍል አንድ

አጠቃላይ ሁኔታዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የለውጥና የልማት ቡድን አደረጃጀት መመሪያ ቁጥር 711/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

1) "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር፣ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሚኒስትር ወይም ሚኒስትር ዴኤታ ማለት ነው፣

2) "የቢሮ ሃላፊዎች" ማለት በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት ተጠሪነታቸው ለሚኒስትሩ ወይም ለሚኒስቴር ዴኤታዎች የሆኑ የቢሮ ሃላፊዎችን ነው፣

3) "የመምሪያ ሃላፊዎች" ማለት በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በመካከለኛ የአመራር ደረጃ የሚገኙና የሥራ ሂደት ፈፃሚዎችን የሚመሩ ተጠሪነታቸው ለቢሮ ሃላፊዎች/ምክትል ቢሮ ሃላፊዎች ወይም ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለሚኒስትሩ የሆኑ የሥራ ሂደት ሃላፊዎችን ነው፣

4) "የለውጥና የልማት ቡድን "ማለት አመራሮችና ፈጻሚዎች የተቀራረበ አመለካከት፣ እውቀትና ክህሎት ኖሯቸው እና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባርን በመናድ የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አመለካከትና ተግባር በማዳበር የተቋሙን ዕቅድ በጋራ የሚያከናውንበትና አፈፃፀምን የሚገማገሙበት አደረጃጀት ነው፣

5) "ልማታዊ አስተሳሰብ" ማለት የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በማስወገድ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታና እሴት በማይጨምር መልኩ እና የልማትና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ውስጥ ሳይሳተፉ በአቋራጭ የመክበር፣ በሙስና፣ በአድልዎና በህገወጥ መንገድ መጠቀምን አምርሮ ለመታገል የሚያስችል በአመለካከትና በተግባር የሚገለፅ አስተሳሰብ ነው፣

6) "አመራር" ማለት በሚኒስቴር መ/ቤቱ መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በተለያየ የዕርከን ደረጃ የሚገኙ አስፈፃሚዎችን/ፈፃሚዎችን አስተባብሮ ወደ ግብ ሥኬት ለመምራት የተደራጀ በሥሩ የታቀፉ አስፈፃሚዎችን/ፈፃሚዎችን የያዘ የተጠያቂነትና የውሳኔ ሰጪነት ሃላፊነት የተሰጠው ከከፍተኛ እስከ ታችኛው የአመራር ዕርከን ድረስ ያለውን የአመራር ስብስብ ያካትታል፤

7) "ፈፃሚ" ማለት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው። ሆኖም ሚኒስትሩን ፣ ሚኒስትር ዴኤታዎችን ፣ ዳይሬክተሮችን ፣ ም/ዋና ዳይሬክተሮችን እንዲሁም በተመሣሣይ ደረጃና ከዚያ በላይ ያሉ የሥራ ሃላፊዎችን አይጨምርም፤

8) "ቢሮ" ማለት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተደራጁ ቢሮዎች፣ ኤጀንሲ፣ ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች እና ጽ/ቤቶች ናቸው።

3. አስፈላጊነት

1) አመራሩና ፈፃሚው እርስ በእርስ በመማማር የአመለካከት ጥራት የሚያመጡበት እና የክህሎት አቅማቸውን የሚገነቡበት የዕርስ በእርስ መማማር ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም በተከታተይነትና በቀጣይነት እንዲተገበር በሚያስችለው አደረጃጀት ባለመደገፉ የለውጥና የልማት ሰራዊት በሚጠበቀው ደረጃ እና ፍጥነት ለመገንባት በማስፈለጉ፤

2) በተግባር እየተፈተነና በዕቅድ አፈፃፀም ሂደት ክፍተቱ እየተለየ እና አቅሙ እየተገነባ ግንባር ቀደም አመራርና ፈፃሚ እንዲሁም ተተኪ አመራር የሚፈራበት አሰራር በማስፈለጉ እና

3) ዕቅድን በጋራ ተቀብሎ የሚፈጽም፣ የሚገመግም፣ በአፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን ለይቶ በወቅቱ የሚፈታ፣ የተሻሉ ተሞክሮዎችን እየለየ አፈፃፀምን ለማጎልበት የሚጠቀም ጠንካራ የአመራሮችና ፈፃሚዎች ቡድን አደረጃጀት በማስፈለጉ ናቸው።

4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ አመራሩና ሠራተኛው በተደራጀ ቡድን ዕቅድን ለማዘጋጀት፣ ለመተግበር እና አፈጻጸምን ለመከታተል የሚችሉበት በትግበራ ሂደቱም እርስ በርስ

በመማማር የአመለካከት እና የክህሎት እቅማቸውን የሚገነቡበት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

1) አመራሩና ፈጻሚው በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት በሚለዩ የአመለካከት እና የክህሎት ክፍተቶች ላይ እንዲሁም የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት እና ተግባር መዋጋትን ማዕከል አድርጎ በመወየያት እና በመማማር በጋራ ጥረት የክህሎት እቅማቸውን እንዲገነቡ የአመለካከት ጥራት እንዲያመጡ ማስቻል ነው፤

2) አመራሩና ፈጻሚው ቀጣይና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በቡድን ዕቅድን እንዲፈጽሙ፤ አፈጻጸምን እንዲገመግሙ፤ በተግባር ሂደት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን እንዲያዳብሩ እና ክፍተቶችን በወቅቱ እንዲያርሙ ማስቻል ነው፤

3) በተግባር አፈጻጸም፤ በአመለካከት ጥራት እና በክህሎት ብቃታቸው የተሻሉ አመራሮች እና ፈጻሚዎችን ለይቶ በማውጣት ተተኪ አመራር ለማፍራት፤ ለማብቃት፤ ዕውቅና ለመስጠትና ለማበረታታት እንዲሁም ዝቅተኛ አፈፃፀም ያስመዘገቡ አመራሮች እና ፈጻሚዎች የተሻለ አፈጻጸም ካስመዘገቡ አመራሮች እና ፈፃሚዎች በመማር አፈጻጸማቸውን እንዲያሻሽሉ ለማድረግ ነው፤

5. የሚጠበቅ ውጤት እና ፋይዳ

1) በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተፈጠረ የጠራ አመለካከት የያዘ፣ ክህሎቱ የተገነባ እና ኪራይ ሰብሳቢነትን አምርሮ የሚጠላ እና የሚታገል ልማታዊ አስተሳሰብና ተግባር ያለው የለውጥ እና የልማት ሠራዊት፤

2) የልማታዊ አመለካከት እና ተግባር በማዳበር ረገድ ራሱን የቀየረ ህብረተሰቡንም መቀየር የሚችል የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አመራር እና ፈጻሚ፤

3) የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አመራር እና ፈጻሚ የተዋህደ እና የጎለበተ የመፈጸም እና የማስፈጸም አቅም አሟጦ በመጠቀም የተገኘ የጎለበተ የዕቅድ አፈጻጸም ደረጃ፤

4) በተግባር ሂደት ተለይተው የወጡ እና የበቁ ተተኪ አመራሮች እና የተቀመሩ እና ለማስፋት የተዘጋጁ ምርጥ የአፈጻጸም ተሞክሮዎች ናቸው።

6. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ በሚገኙ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት፡

የለውጥና የልማት ቡድን አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት

7. የአደረጃጀት ሁኔታ

1) በየቢሮው የለውጥና የልማት ቡድን የማደራጀት ዋነኛ ኃላፊነት የቢሮ ኃላፊው ሆኖ ከመምሪያ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር የሚፈጽመው ይሆናል፤

2) የለውጥና የልማት ቡድን የተቋሙን መደበኛ አደረጃጀት መሠረት በማድረግ በየደረጃው የሚደራጅ ይሆናል፤ በዚህም መሠረት በየቢሮዎች ውስጥ እንደሚገኘው የሰው ኃይል ብዛት ቁጥራቸው የሚወሰን የለውጥና የልማት ቡድኖች ይደራጃሉ። ስለዚህ የለውጥና የልማት ቡድን አደራጃጀት ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይሆናል፤

ሀ) በአንድ መምሪያ ውስጥ ያሉ ፈጻሚዎች በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ የፈጻሚዎች የለውጥና የልማት ቡድን ሥር ይደራጃሉ፤

ለ) የለውጥና የልማት ቡድን የሚደራጀው በእቅድ በተያዙ ተግባራት ዙሪያ ስለሆነ ተያያዥነት ያላቸው ተግባራትን የሚያከናውኑ ፈፃሚዎች በአንድ ቡድን ውስጥ የሚደራጁ ሆኖ የአባላቱ ብዛት ቢያንስ ሦስት ቢበዛ አስር ይሆናል፤

ሐ) የለውጥና የልማት ቡድን አስተባባሪ የመምሪያ ኃላፊ ይሆናል፤

መ) የለውጥና የልማት ቡድን አባላት አስተባባሪ የመምሪያ ኃላፊው ነው። ሆኖም በአንድ መምሪያ ውስጥ የሚሰሩ ፈጻሚዎች ቁጥር ከ10 በላይ ከሆነ ለመምሪያ ኃላፊው ተጠሪ የሆኑ ተጨማሪ ቡድኖች ይቋቋማሉ፤

ሠ) ከአንድ በላይ የለውጥና የልማት ቡድን ባለበት መምሪያ በተጨማሪ ለሚቋቋሙት ቡድኖች የሚመደበው አስተባባሪ የሚመረጠው በፈጻሚዎች ሆኖ በመምሪያ ኃላፊው እና በቢሮ ኃላፊው አስተያየት ተስጥቶበት የሚጸድቅ ይሆናል፤

10) የቡድኑ አባላት ሳምንታዊ እና የዕለታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ፣ የአፈፃፀማቸውን እንዲመዘግቡ እና የአፈፃፀም ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ፤

11) የፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት ትግሉን በጽናት መደገፍ፣ ሴክተሩ የሚሰጠውን ተልዕኮ በብቃትና በላቀ ውጤት መፈፀምና ለለውጥና ልማት ሰራዊት ግንባታ የበኩላቸውን ሚና መወጣት፤

12) በየጊዜው በሚያረጉ የተግባራት አፈፃፀም ግምገማ የቡድኑ አባላትን አፈፃፀም ደረጃ ማውጣት እና የተሻለና የላቀ የአፈፃፀም ውጤት ያስመዘገቡ ግንባር ቀደም ፈፃሚዎችን መለየት፤

13) በየወሩ፣ በሩብ ዓመቱ እና በግማሽ ዓመት የመምሪያው የውጤት ተኮር ዕቅድ፣ እራስን የማብቃት ዕቅድ እና የዙሪያ መለስ አፈፃፀም ግምገማ ፕሮግራም ላይ በመገኘት የነቃ ተሳትፎ ማድረግ፤

9. የለውጥና የልማት ቡድን አስተባባሪ ተግባርና ኃላፊነት

1) ቡድኑን ያስተባብራል፤ የቡድን የውይይት መድረክ በበላይነት ይመራል፤

2) የቡድኑ አባላት በሙሉ እራስን የማብቃት ዕቅድ አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በማድረግ ገምግሞ ያጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

3) ከውይይቱ ጊዜ አንድ ቀን አስቀድሞ የሳምንቱን የዕቅድ አፈፃፀም አቅጣጫ እና ሌሎች የውይይት አጀንዳዎችን በማዘጋጀት ለቡድኑ አባላት እንዲደርስ ማድረግ፤

4) ከአንድ በላይ የለውጥና የልማት ቡድን ባለበት መምሪያ ለተጨማሪ ቡድኖች የተመደበው አስተባባሪ የቡድኑን የሳምንቱን የዕቅድ አፈፃፀም አቅጣጫ እና ሌሎች የውይይት አጀንዳዎችን በማዘጋጀት ለቡድኑ አባለት እንዲደርስ ከማድረጉ በፊት ከመምሪያው ኃላፊ ጋር መወያየት ይኖርበታል፤

5) የቡድን ውይይት ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ፍሬያማ እንዲሆንና ለለውጥና ለልማት ሰራዊት ግንባታ መሰረት እንዲሆን የሚያስችሉ ስልቶችን በመቅረጽ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

6) የቡድኑን አባላት የውይይትና የአፈፃፀም ሪፖርት በማቀናጀትና በማደራጀት ለመምሪያው ኃላፊ ሪፖርት ያደርጋል፤

7) የቡድኑን አባለት የስራ አፈፃፀም መረጃ በቅፅ 002 እና 003 መሰረት አደረጅቶ ይይዛል፤

8) ከራሱ እና ከቡድኑ አቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ከአመለካከት፤ ከግብዓት፤ ከክህሎት ወዘተ አንጻር በመለየት ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና የሥራ ክፍሎች ጋር በመሆን እንዲፈቱ ያደርጋል፤

9) ከቡድኑ አባላት በየግማሽ ዓመቱ የሚለወጥ ፀሐፊ በመሰየም የቡድኑን ቃላ ጉባኤ በቋሚ መዝገብ ተደረጅቶ እንዲያዝ ያደርጋል፤

10) ለቡድን አባላት በተናጠልና በጋራ በየጊዜው ግብረ መልስ ይሰጣል፤

10. የመምሪያ ኃላፊ

1) ቡድኑን ያስተባብራል፤ የቡድን የውይይት መድረክ በበላይነት ይመራል፤

2) በመምሪያ ውስጥ ከአስር የሚበልጡ ፈጻሚዎች ካሉ ከቢሮ ኃላፊ ጋር በመሆን በመምሪያ ደረጃ የፈፃሚዎች የለውጥና ልማት ቡድን ያደራጃል፤

3) የመመሪያውን የለውጥና የልማት ቡድን መረጃ በቅፅ 001 እና 002 መሰረት አደራጅቶ ይይዛል፤

4) በየሣምንቱ መጨረሻ የየሳምንቱ የለውጥና ልማት ቡድን የዕቅድ እና የአፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ይገመግማል፤ ያጋጠሙ ችግሮችን፤ የተፈቱበትን አግባብ፤ ትኩረት የሚያሻቸውንና ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ወዘተ ለይቶ የያዘ የተጠቃለለ ሪፖርት በየወሩ ለቢሮ ኃላፊ ያቀርባል፤

5) በሳምንታዊ የቡድኖች አፈፃፀም ግምገማ የተለዩ ክፍተቶችንና ማነቆዎችን የሚፈቱበትን ስልት ይነድፋል፤ይተገብራል ስለአፈፃፀማቸው ለቢሮ የተተነተነ ሪፖርት ያቀርባል፤

6) ቡድኑ በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ውይይት መካሄዱን ይከታተላል፤ከውይይቱ አንድ ቀን አስቀድሞ በመምሪያ ውስጥ ከአንድ ቡድን በላይ የተደራጀ ከሆነ ከቡድን አስተባባሪዎች ጋር በመሆን የሳምንቱን የዕቅድ አፈፃፀም አቅጣጫ እና ሌሎች የውይይት አጀንዳዎችን በማዘጋጀት ለቡድኑ አባላት እንዲደርስ ያደርጋል፤

7) የቡድኑ አፈፃፀምና አሰራር ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ፍሬያማ እንዲሆንና ለለውጥና ለልማት ሰራዊት ግንባታ መሰረት እንዲሆን የሚያስችል አመራር ይሰጣል፤

8) የለውጥና የልማት ቡድን መድረክ ውይይት ጉድለቶች መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች ቶሎ መፍትሔ እንዲያገኙና የተወሰኑ ውሳኔዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያስተባብራል ያስፈጽማል፤

9) የቢሮ አመራሮች የለውጥና የልማት ቡድን አባል በመሆን ለቢሮ ዕቅድ አፈፃፀም ስኬት ድርሻውን ይወጣል፤

11. የቢሮ ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

1) ከመምሪያ ኃላፊዎች ጋር በመሆን የፈፃሚዎች የለውጥና ልማት ቡድን ያደራጃል፤

2) የለውጥና የልማት ቡድኖች መድረክ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በቀጣይነትና በተከታተይ መካሄዱን ያረጋግጣል፤

3) የቡድኑ አፈፃፀምና አሰራር ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ፍሬያማ እንዲሆንና ለለውጥና ለልማት ሰራዊት ግንባታ መሰረት እንዲሆን የሚያስችል አመራር ይሰጣል፤

4) የለውጥና የልማት ቡድን መድረክ ውይይት ጉድለቶች መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች ከአመለካከት፣ ከክህሎት፣ ከግብዓት፣ ከክትትልና ድጋፍ ወዘተ አንጻር አደራጅቶ መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ በቡድኖቹ፣ በራሱና በበላይ አመራሮች የተላለፉ ውሳኔዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያስተባብራል ያስፈጽማል፤

5) በቢሮ ደረጃ የአመራሮች የለውጥና የልማት ቡድን ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ ሩብ ዓመት እና ግማሽ ዓመት የአፈፃፀም ግምገማ መድረክን ይመራል፤

6) በየሣምንቱ መጀመሪያ የለውጥና የልማት ቡድኖችን (የቢሮውን የሥራ አመራር ኮሚቴ) የየሳምንቱ የዕቅድ እና የአፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ከመምሪያ ኃለፊዎች ጋር ይገመግማል ፤

7) በየወሩ የቢሮውን የቡድን የአፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ተደራጅቶ ለማስፈፀም አቅም ግንባታና ለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ እና ተጠሪ ለሆኑበት ሚኒስትሮች እንዲቀርብ ያደርጋል፤

8) የቡድኖችን አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት መሰረት በማድረግ ለመምሪያዎች ግብረ መልስ ይሰጣል፤

12. የማስፈፀም አቅም ግንባታና የለውጥ ስራ አመራር ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

1) የማስፈፀም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ ለውጡን እንዲመራ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ የለውጡ አካል በማድረግ በሁሉም ደረጃ የሚደርገው የለውጥና ልማት ቡድን መድረክ እንቅስቃሴ አፈፃ ፀምና የሚገኝበትን ደረጃ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ይገመግማል፤ አካሄዱ ላይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤ ግብረመልስ ይሰጣል፤

2) የለውጥና ልማት ቡድኖች አፈጻጸም ሪፖርት በየወሩ በማጠናቀርና በየ6ወሩ በመገምገም ለሚኒስትሩና ሚኒስትር ዴኤታዎቹ ያቀርባል፤

3) የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የለውጥና ልማት ቡድን አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ያዘጋጃል፤ ያሻሽላል፤በመመሪያው ላይ ስልጠና ይሰጣል፤

13. የሚኒስትር ዴኤታ ተግባርና ኃላፊነት

1) በዘርፉ የሚመራቸውን የለውጥና የልማት ቡድን ያደራጃል፤ይመራል ያስተባብራል፤

2) የቡድኑ አፈፃፀምና አሰራር ቀልጠፋ፣ ውጤታማ እና ፍሬያማ እንዲሆንና ለለውጥና ለልማት ሰራዊት ግንባታ የበኩሉን እንዲወጣ የሚያስችል አመራር ይሰጣል፤

3) የለውጥና የልማት ቡድን መድረክ ውይይት የተለዩ ክፍተቶች እና ማነቆዎች መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች አፋጣኝ መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የተወሰኑ ውሳኔዎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ ይከታተላል፤

4) በየወሩ የዘርፉን የቡድኖች የአፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት ተደራጅቶ ለሚኒስትሩ እንዲደርስ ያደርጋል፤

5) የቡድኖች አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት መሰረት በማድረግ ለበረሮዎች ግብረ መልስ ይሰጣል፤

6) በየወሩ የሚቀርበውን የቡድኖች አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት መሰረት በማድረግ ቀጣይ አቅጣጫ ያሰቀምጣል፤ ማነቆዎችን ይፈታል፤ ቀጣይ የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

14. የሚኒስትር ተግባርና ኃላፊነት

1) የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የለውጥና ልማት ቡድን አደረጃጀት መመሪያ ያጸድቃል፤

2) የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የቡድን ውይይት የጊዜ ሰሌዳ ያጸድቃል፤

3) በቡድኖች አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት መሰረት ቀጣይ የአፈፃፀም አቅጣጫ ያሰቀምጣል፤ ማነቆዎችን ይፈታል፤ ቀጣይ የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

ክፍል ሦስት

የለውጥና ልማት ቡድን አሰራር ሁኔታ እና አካሄድ

15. የውይይት ጊዜ ሰሌዳ

1) የፈጻሚ የለውጥና የልማት ቡድን የውይይት ጊዜ በሳምንት አንድ ቀን አርብ ዕለት ከቀኑ 10:30 — 11:30 የሚካሄድ ይሆናል፤

2) የውይይት ማድረጊያ ጊዜ በተራ ቁጥር 3.1.1 እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ባህሪቸው ለውጭ ተገልጋይ አገልግሎት መስጠት የሆነ ቡድኖች የውይይት ሰዓታቸውን አገልግሎት አሰጣጡን በማይበድል ሁኔታ በማስተካከል ለማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ አትርበው ያጸድቃሉ፤ ተለዋጭ የውይይት ጊዜ ከሥራ ቀን ውጪ ከሆነ ለቡድኑ አባላት የትራንስፖርት አገልግሎት ክድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ ጋር በመሆን መመቻቸት ይኖርበታል፤

3) በበዓላት ወይም ከግማሽ በላይ የሆነ የቡድኑ አባላት ባስገዳጅ ምክንያት በስራ ገበታቸው ያልተገኙ ከሆነ ተለዋጭ ፕሮግራም በማዘጋጀት ውይይቱ የሚካሄድ ይሆናል፤ ተለዋጭ ፕሮግራሙ ከሥራ ቀናት ውጪ ከዋለ የትራንስፖርት አገልግሎት ክድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ ጋር በመሆን መመቻቸት ይኖርበታል፤

4) የለውጥና የልማት ቡድን ውይይት ከተያዘለት ሰዓት በላይ መውሰድ የለበትም፤ ሆኖም ቡድኑ የያዘው አጀንዳ ተጨማሪ የውይይት ሰዓት የሚያስፈልገው መሆኑን አባላቱ ካመኑበት በስምምነት ሊያራዝሙት ይችላሉ፤

16. የውይይት መድረኩ አካሄድ እና አፈፃፀም

1) የለውጥና የልማት ቡድን ውይይት በዴሞክራሲያዊ አግባብ የሚካሄድ ይሆናል። በመሆኑም ከእለቱ አጀንዳ ጋር በተያያዘ አባላት በነፃነት ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡና እንዲወያዩበት ይደረጋል።በውይይት መድረኩ የቡድኑን አባላት ተሳትፎ የሚገድብ ተግባር በቡድኑ አባላትም ሆነ በሌሎች አካላት መፈጸም የተከለከለ ነው፤

2) በለውጥና የልማት ቡድን ዋነኛው የውይይት አጀንዳ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን በቅንጅት፣ በመደጋገፍ እና በመናበብ በላቀ ደረጃ መፈጸም ነው። በመሆኑም በቡድኑ የውይይት መድረክ፤

ሀ) የቡድኑ የተጠናቀቀው ሳምንት አፈጻጸም እና የቀጣይ ሳምንት ዕቅድ ላይ በመወያየት እያንዳንዱ የቡድኑ አባል በሥራ መደቡ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እና በግብ ተኮር ተግባራት ተመንዝሮ የወረደለትን ዕቅድ ታሳቢ ያደረገ የዕቅድ ክፍፍል ይደረጋል፤ በተጠናቀቀው ሳምንት የነበረው አፈጻጸምም ይገመገማል፤

ሰ) ጠንካራ አፈጻጸም ያለው ፈጻሚ ተሞክሮውን ያካፍላል፤ ደካማ አፈፃፀም ያለው ፈፃሚ በግሉና በባልደረቦቹ ተገምግሞ አፈጻጸሙ ደካማ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ይለያል፤ ለችግሩ ማስተካከያ አቅጣጫ ይቀመጥለታል፤

ሐ) በግምገማ በተለዩ የአመካከትና የክህሎት ክፍተቶች፤ በመንግስት እና በተቋሙ በሚወጡ ተያያዥነት ያላቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና የህግ ማእቀፎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት በሚያዘጋጁት ርዕሶች ላይ በመወያየት የአባላቱን አቅም የመገንባት ተግባር ይከናወናል፤

3) የለውጥና የልማት ቡድን ውይይት የቡድኑን ተልዕኮ መሠረት ባደረገ፣ የትኩረት ማዕከሉን ባልሳተና ባልተንዛዛ፣ አፈፃፀምና ውጤትን ለማሻሻል በሚያስችል፣ አባላት ለመማማርና ለቡድንም ሆነ ለግል ስብዕና ዕድገት ግብዓት ለማግኘት በጉጉት በሚጠብቁት ሁኔታ ይመራል፤

4) የለውጥና የልማት ቡድን ውይይት ሂደት እና ውጤት አገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻልና የተገልጋይ እርካታን ለማረጋገጥ እንጂ የቡድኑን ውሀደት የሚሸረሽር መሆን የለበትም፤

17. የለውጥና የልማት ቡድን መረጃዎች አያያዝ ሁኔታ

1) የለውጥና የልማት ቡድን አደረጃጀት መረጃ በቅጽ 001 መሰረት ተዘጋጅቶ ቡድኑ ተጠሪ ለሆነበት መምሪያ፣በቢሮው እና በማሰፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ስራ አመራር ቢሮ ተደራጅቶ ይያዛል፤

2) የለውጥና የልማት ቡድን አባላት ሳምንታዊ አፈጻጸም በቅፅ 003 መሰረት ተዘጋጅቶ በየወሩ ቡድኑ ተጠሪ ለሆነበት መምሪያ ይቀርባል፤

3) የለውጥና የልማት ቡድን ውይይት ቃለ ጉባዔ በውይይቱ የተነሱ ጉዳዮች፣የተለዩ ጥንካሬዎችና ድክመቶች፣የተላለፉ ውሳኔዎች ወዘተ በማጠቃለል ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ቅፅ 003 መሰረት ተዘጋጅቶ በመምሪያው ተደራጅቶ ይያዛል፤

4) የመምሪያ ኃላፊ በስሩ ያሉ የለውጥና የልማት ቡድን/ኖች አደረጃጀት መረጃ በቅፅ 001፤ ሳምንታዊ የአፈጻጸም ደረጃ ማጠቃለያ ቅፅ 002 እና ሳምንታዊ ቃላ ጉባዔ፤

የቡድኑ የውይይት ቃለ ጉባዔዎች ተደራጅቶ እንዲያዝ በማድረግ ለወርሃዊ የአፈፃፀም ግምገማ በግብዓትነት ይጠቀምበታል።

18. የማንኙነት አግባብና ሪፖርት

1) የለውጥና ልማት ቡድን አስተባባሪዎች በየሣምንቱ መጨረሻ በየቡድኑ የተደረገውን ውይይት እና የተደረሰበትን ድምዳሜ ከመምሪያው ኃላፊ ጋር በመሆን ይገመግማሉ።

2) በመምሪያ ደረጃ ወርሃዊ የቡድን አፈፃፀም ግምገማ በማጠቃለል የመምሪያው ኃላፊ ለቢሮ ኃላፊው በቅፅ 004 መሰረት ሪፖርት ያደርጋል።

3) በቢሮ ደረጃ ወርሃዊ የቡድን አፈፃፀም ግምገማ በማጠቃለል ለማስፈፀም አቅም ግንባታና ለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ በቅፅ 005 መሰረት ሪፖርት ያደረጋል።

4) የሁሉም ቢሮዎች የቡድን አፈፃፀም ግምገማ ውጤታማነት የማስፈፀም አቅም ግንባታና ለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ የተጠቃለለ ሪፖርት በቅፅ 005 መሰረት በየወሩ ለሚኒስትሩ እና ሚኒስትር ዴኤታዎቹ በማቅረብ እንዲገመገም ይደረጋል።

5) በየደረጃው ያሉ ሪፖርት የሚቀበሉ አካላት ለሪፖርት አቅራቢው አካላት ወቅታዊና ተገቢ ግብረ-መልስ ይሰጣሉ።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

19. የለውጥ እና ልማት ቡድን የማስፈፀም ኃላፊነት

የለውጥና ልማት ቡድን መድረክ በማጠናከር ተልዕኮው እንዲሳካ የመምራት ኃላፊነት የተቋማት የበላይ ኃላፊ ይሆናል።

20. የፆታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለጹት ሃሳቦች በሙሉ በተመሳሳይ የሴት ፆታንም የሚያመለክቱ ይሆናሉ።